# ሰሞኑን በፓልቶክ ቁጥር 9
# የተሞላ አሻንጉሊት
# ከበልጅግ አሊ

በሳምንቱ ማለቂያ ላይ ወደ ፓልቶክ ጎራ ማለቴ የማይቀር ነው። ጎራ ካልኩ ደግሞ የቴያትሩ አዳራሽ የሆነውን የደደቦች ሸንጎ ሳልጎበኝ አላልፍም። የስድብ መላኪዬንም መመልከቴ አይቀርም። በደደቦች ሸንጎ የንፁህ ኢትዮጵያዊነት ማዕረግ የተገፈፉት ቁጥር ጨምሮአል። ኢሕአፓ፣ አያሌው ውንዴሳ፣ ሃይሉ ውርጌሳ፣ ዶክተር ታዬ ፣ ሻለቃ ዮሴፍ ሌሎችም፣ ሌሎችም እንዲሁ።  በታላቁ የደደቦች ሸንጎ ሙሉ መጠየቂያውን በማሟላት በፈለገ ጊዜ መጥቶ እንዲያስረዳ የተፈቀደለት ዳዊ ኢብራሂም ሆኗል። ይህንን እድል እስከ አሁን ያገኙ አንዳርጋቸው ፅጌና ብርሃኑ መዋ ብቻ ነበሩ። ይህ የሆነበት ምክንያት ፀረ ኢሕአፓ አቋሙ ከኤርትራም ከወያኔም ሊያሰራው እንደሚችልና በደርግ አሰፓ አባሎች ክፍተኛ ግምት አግኝቶ ነው።

በደደቦች ሸንጎ የተደረገው የዳዊ ኢብራሂም ቃለ መጠይቅ በኤርትራና በወያኔና በደርግ እርዝራገሮች በፀረ ኢትዮጵያ፣ በፀረ ኢሕአፓ ላይ ሰሞኑን የተከፈተው ጦርነት ቅጣይ ነው። ቃለ መጠይቁን ትመራ የነበረችው ጨካኙዋ ብዙ ወንድማገኝ ስትሆን ይህችን ግለሰብ ደጋግሜ እንደገለፅኩት የቀይ ሽብር ቀንደኛ፣ ከማጀት ወደ አደባባይ የሚል ፕሮግራም በኢትዮጵያ ራዲዮ አዘጋጅ ፣ ከፍተኛ የኢሰፓ አባልና ፣የደርግ ጋዜጠኛ የነበረች ነች።

ቃለ መጠይቁ ለማንም የተፈቀደ ቢሆንም መጠይቅ የሚችሉት ግን በክፍሉ ታማኝነታቸው የተረጋገጠው ብቻ ናቸው። ከዳዊ ጋር ይሰሩ የነበሩ የሰራተኛ ማሕበር ተመራጮች አሳቡን ለመቃወም ተከልክለዋል። የተሰጠው ምክንያት ዳዊ ማንንም የሱ ተቃዋሚ ወይም እውነቱን አጋላጭ መስማት አልፈልግም ብሎ በጠየቀው መሰረት ነው። ዳዊ ወንድሞቼ ነበሩ የሚላቸውን ሁሉ ለመሰማት ፍላጎት የለውም። እነዚህ ግለሰቦች ብዙ ሚስጥር ስለሚያውቁ ያጋልጡኛል የሚል ፍርሃት ያለበት ይመስለኛል ።

ዳዊ ከኢሕአፓ ጋር ያለው ግንኙነት ሲያስረዳ  ድሮ ወጣት ሳለ የባሌ ተወላጅ ሆኖ ትግራይ መሸፈቱን በመገረም ነበር ያቀረበው። ኢሕአፓ ውስጥ የገባው በልጅነት ተሳስቶ ስለሆነ ለደደቦች ሸንጎ ለሚገኙት የደርግ ኢሰፓ አባላት የይቅርታ አቤቱታውን አቅርአቦል። ወደፊት ስልጣን ላይ ስትመለሱ በተቀሩት የኢሕአፓ አባለት ላይ ቀይ ሽብር ስትጀምሩ፣ ፍርድ ስታቀርቡ ምስክርም እሆናለሁ ብሎ ማስተማመኛ ሰጥቷል። በዛውም ከኢሕአፓ ሸሽቼ ወደ ደርግ ስቀላቀል በመንግስቱ ኃይለማርያም የተፈረመ የምህረት ደብዳቤ ስለሚገኝ ያንን ላቀርብ እችላለሁ በማለት አስረድቷል። ስለዚህ ወደፊት ምህረት እንደሚገኝ ከወደዚሁ ቃብድ ተቀብሎአል።

ከኢሕአፓ ጋር ያለኝ ችግር በግልና በቤተሰብ አካባቢ ነው ያለው ዳዊ የችግሩ መንስኤ የፖለቲካ ሳይሆን የግል ነው ብሎም አስረድቷል። ኢሕአፓ በግል ሕይወታችን እንኳ ስለምትገባ ተጠንቀቁ የሚል ማስጠንቀቂያ ተናግሯል። ባለቤቱን በከፍተኛ ደረጃ ሲደበድብ ነበር ተብሎ የሚታማው ዳዊ ምንም እንኳ በሴቶች እኩልነት ታምናለህ ወይ ተብሎ እንዲጠየቅ በመድረኩ ላይ ቢፃፍም አዘጋጆቹ ያንን ለመጠየቅ ምንም ፍላጎት ስላልነበራቸው ብዙ ወንድምአገኝሁን እየደወሉ እንድትጠይቀው ቢለምኑዋት እንኳ ለብዙ ግዜ ስለሴቶች ታገልኩ የምትለው ይህች ግለሰብ ጥያቄውን የኢሕአፓ ነው በማለት ከመጠየቅ ስልኳን አሽቀንጥራ መጣልን መርጣለች።

ዳዊ በግል ኢ.ሕአፓ በፈጠረብኝ ችግር እራሴን ለማጥፋት አስቤ ነበር ብሎ ከዛም ቀጥሎ ዛሬ ከእናንተ ጋር እንድደባለቅ ስለተፈቀደልኝ አመሰግናለው በማለቱ በደደቦች ሸንጎ ከታወቁት ተሳዳቢዎች ብርቅ የደደቦች ሸንጎ አባል ተብሎ እስከመሰየም ደርሷል። ብዙዎቹ የደርግ ኢሰፓ አባላት የቀይ ሽብር ጥሪ ግዜ እንደተደሰቱት አሁንም ጮቤ ሲረግጡ ታይተዋል። የኢ.ሕአፓን ስስ ብልት አገኘን በማለት ቦዘኔያዊ ትንተናቸውን ሲያሰሙም ነበር።

የሆነ ሆኖ አንዳንድ አይጠፉምና ሰላም ሁኑ የሚባል የዛ ክፍል አባል ዳዊን በቀጥታ ከወያኔ ጋር ግንኙኝነት አለህ ተብሎ በሰፊው ይነገራል። ይህ ደግሞ የኢ.ሕአፓ ስም ማጥፋት ሳይሆን በሆላንድ የማውቃቸው በዚህ ክፍል የሚገኙ አባሎቻችን ሳይቀሩ የነገሩን ነው፤ ይህ እውነት ነው ውሸት ለሚለው ጥያቄ በቀጥታ ውሸት ነው የሚል መልስ መስጠት ያልፈለገው ዳዊ ነፍሱን ይማረውና የተፈራ አስማረን አስከሬን ወደ ሃገሩ ለመላክ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጋር መስራት ስለነበረብኝ ከብዙ ሰዎች ጋር እገናኝ ነበር። በዚህ ምክንያት ነው ግንኙነቴ የጀመረው በሚል መልሷል። በፀረ ወያኔ ትግሉ ውስጥ አለህበት ወይ የሚለውን ሳያነሳውም አልፎል።

ግለሰቡ በተደላደለ መድረክ ላይ በተዘጋጀ ጥያቄ ሲቀባጥር አምሽቷል። ይህ መድረክ ምን ግዜም ነፃ እንደማይሆን እናውቃለን። ታዲያ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ድረኮች ምን ይጠበቃል።

1ኛ. ከወያኔስ ጋር ቅርብ ግንኑነታ አለው?
2ኛ. ፎረም 84 የሚባለው የወያኔ ድርጅት አባል ነው?
3ኛ. በንዋይ አጥፊነትስ የሚጠየቅበትስ አለ?
4ኛ. የኢ.ሕአፓ አባላትን በአዲስ አበባ በማስያዝ ተሳትፎአል?
5ኛ. ከደርግ ጋር ሆኖ የቀድሞ ጓዶቹን ነፍስ አጥፍቶአል?

እነዚህንና የመሰሉትን ጥያቄዎች ሕዝብ እንዲያውቃቸው ስለሚያስፈልግ

1ኛ. አብረውት የነበሩ የሰራተኛ ማህበር አባላትን
2ኛ. በሚኖርበት አካባቢ የሚኖሩ ታዋቂ ግለሰቦችን
3ኛ. ባለቤቱን ከተቻለ

ለህዝብ ቀርበው እንዲስረዱ ካልተደረገ በስተቀር የሚናገረላቸው የሌላቸው በዳዊ የግፍ ተግባሮች የተበደሉ ሁል ግዜ እንደተጎዱ ይቀራሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ በሴቶች እኩልነት አለማመን ፣ ሚስትን መደብደብ ፣ ከፖለቲካ ስራ ሊያስገልልም ይገባል።ይህ የኢ.ሕአፓ ወይም የሆላንድ ሴቶች ጥያቄ ብቻ ሊሆን አይገባውም። የማናቸውም ዴሞክራት ጥያቄም ነው። አንዳንዶቻችሁ የቤተሰብ ችግር ወደ ፖለቲካ ሊለወጥ አይባውም ልትሉ ትችላላችሁ። እኔም ይህንን አምንበታለሁ። የእህቶቻችን መብት ግን የግለሰብ ብቻ ሳይሆን የሆላችንም ጥያቄ መሆኑን አልጠራጠርም። ስለዚህ እነዚህ በህብረተስብ ውስጥ የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ተጨምረው ነው ለመሪነት ብቁ የሚደርጉን።

ኢ.ሕአፓን መስደብ በኢሰፓና በወያኔ አባላት ሊያስወድድ ይችላል። ግን በኢትኢዮጵያ ህዝብ ደግሞ ጥላቻን ይፈጥራል፡፡ ብዙ ግለሰቦች ኢ.ሕአፓን በመስደብ የኢሰፓውን ድጋፍ ካገኙ በኃላ ለወያኔ አድረዋል።ክህደቱ ለምሰሌ መጥቀስ ጥሩ ነው።የደደቦች ሸንጎን በፀረ ኢ.ሕአፓ ወያኔ ሲጠቀምበት የመጀመሪያው አደለም። የወያኔ የፓልቶክ ክፍል አላፊ አባ መላ አፐሪል በሚል መጠርያ የቅንጀት አባል ሆኖ ጸረ

ኢ.ሕ.አ.ፓ ቅስቀሳ ሲደርግ እነደነበር የምናስታውሰው ነው። ከዛው ጋር በመያያዝ ጀነራል ዚ እንደዚሁ መድረክ ተሰጥቶት ኢትዮጵያዊነትንና ኢ.ሕ.አ.ፓን ሲሰድቡ ብዙዎቹ የዛ መድክ አባላት በጸረ ኢ.ሕ.አ.ፓ እንጂ በፀረ ወያኔነት ስላልተሰባሰቡ በአበባ ነበር ቀንደኛ ወያኔዎችን የተቀበሏቸው። አሁን ደግሞ የወያኔ የሆላንድ ተወካይ ይህንን ቢያቀነባብር ምን ይደንቀን ።

ከኛ ታዲያ ምን ይጠበቃል። ሃገራችንን ለማዳን ሆድ አምላኩ ሆነው ካገኙት ጋር እየተኙ ሃገራችንን የሚያደሙትን አንድ በአንድ ማጋለጥ ፣ የስም ዝርዝራቸውን ለህዝብ ማቅረብ ሌላውን እንዳያወናብዱ ለማድረግ ስለሚቻል በዚህ በኩል ጥረቱ ሊቀጥል ይገባል።

ዳዊ የተሞላ አሻንጉሊት ነው። በእሱ ላይ ትኩረት መስጠት አያስፈልግም። ዋናው ከኋላው ሆኖ እሱን የሚያሽከረክረውን ወያኔን መታገል ነው። ወያኔ ሲወድቅ ዳዊና መሰሎቹ ይወድቃሉ። ስለዚህ ከአሻንጉሊቱ ጋር ሳይሆን ከአሽከርካሪው ጋር ያለው ትግል ይቀጥል። ብዙ ሆዳሞችን ወያኔ እንደሚያመጣ አልጠራጠርም። እነርሱም ፀረ ኢ.ሕ.አ.ፓ ይሆናሉ። በእጁ ላይ ደ ያለበት ሁሉ ደግሞ ያረግድላቸዋል። ከዛም ወያኔ በገንዘብ ይገዛቸዋል። ይህንን ከዚህ በፊት ያየነው ፣ የሰማነው ፣ የምናውቀው ነው። ማነው ባለተራ የሚጠመቅ በደደቦች ሸንጎ የወያኔ የጓዳ ወዳጅ ብሎ መጠበቅ ነው።

በቅርብ የሌሎቹን ቃለ መጠይቅ እንደምንሰማ በማመን ለዛሬው በደህና ሰንብቱልኝ።